# ኢትዮጵያ፤ መጪዋ “የአፍሪካ አንበሳ!”

ብ. ነጋሽ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት የአገሪቱን ኢኮኖሚ ሁሉንም ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል፣ ኢኮኖውን ከማሳደግ ጋር ተያይዞ መዋቅራዊ ሽግግር (ከግብርና ወደ ኢንደስትሪ መር ኢኮኖሚ) ማምጣት የሚያስችል የልማት ዕቅዶችን አውጥቶ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። በዚህም ባለፉት አስር ዓመታት ተከታታይ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ ተችሏል። ባለፈው ዓመት ግን፤ ኤልኒኖ ያስከተለው ድርቅ የግብርናውን ዘርፍ እድገት ከነበረበት 6 ነጥብ 6 በመቶ ወደ 2 ነጥብ 3 በመቶ እንዲያሽቆለቁል በማድረጉ የተመገበው የኢኮኖሚ እድገትም 8 በመቶ ብቻ ሆኗል። ያም ሆኖ ግን አገሪቱ አሁንም በፈጣን እድገት ውስጥ ትገኛለች።

የባለፉትን ዓመታት የአገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ለማየት ያህል ከ2003 እስከ 2007 ዓ.ም ተግባራዊ የተደረገውን የመጀመሪያውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈጻጸም በመጠኑ እናስታውስ። የእድገትና ትራንስፎርሜሽኑ ዕቅድ ተግባራዊ በሆነባቸው አምስት ዓመታት፣ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በአማካይ 10 ነጥብ 1 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል። በዚሁ ጊዜ ውስጥ በግብርናው ዘርፍ በየዓመቱ በአማካይ 6 ነጥብ 6 በመቶ ዕድገት ተመዝግቧል። በኢንዱስትሪ ዘርፍ 20 በመቶ እንዲሁም፤ በአገልግሎት ዘርፍ 10 ነጥብ 7 በመቶ አማካይ ዕድገት ተመዝግቧል። ይህ የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት በዕቅዱ ከተቀመጠው ግብ አንፃርና በሌሎች ፈጣን ዕድገት ከተመዘገበባቸው አገራት ኢኮኖሚ አንፃር ሲታይ የተሳካ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

እርግጥ የተመዘገበው ዕድገት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ተይዞ የነበረውን የኢኮኖሚ መዋቅር ለውጥ በሚፈለገው ልክ ማረጋገጥ አላስቻለም። ሆኖም የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው ያለው ድርሻ በ2003 ከነበረበት 10 ነጥብ 3 በመቶ ወደ 14 ነጥብ 3 በመቶ በማደጉ መሻሻል ታይቷል።

በዕቅዱ የተገኘው የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረተ ሰፊና በርካቶችን ተጠቃሚ ያደረገ ነው። የዜጎች የገቢ አቅም እንዲሻሻልና ድህነት በዚያው ልክ እንዲቀንስ ማድረግ አስችሏል። በተመዘገበው ፈጣን ዕድገት የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ፤ በ2003 ከነበረበት 396 የአሜሪካን ዶላር፤ ወደ 632 የአሜሪካን ዶላር ከፍ ብሏል። ይህም አገሪቱን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለማሰለፍ የተያዘውን ራዕይ ማሳካት እንደሚቻል ያመላከተ ነው። በዕቅዱ የትግበራ ዘመናት ተግባራዊ በተደረጉ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ለኅብረተሰቡ በርካታ የሥራ ዕድሎች ተፈጥረዋል። የኅብረተሰቡንም የገቢ አቅም ማሳደግ ተችሏል። በዚህም መሠረት፤ በ1997 ዓ.ም 38 ነጥብ 7 በመቶ የነበረው የድህነት ምጣኔ፣ በ2003  ወደ 29 ነጥብ 6 በመቶ ዝቅ ማለቱን በቤተሰብ ገቢና የፍጆታ ወጪ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የተካሄደ የድህነት ዳሰሳ ጥናት አመላክቷል። ከ2004 ዓ.ም ወዲህም በተከታታይ የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት የድህነት ምጣኔው እንዲቀንስ ማድረግ አስችሏል። የመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ትግበራ በተጠናቀቀበት 2007 ከድህነት ወለል በታች ያለው ህዝብ ወደ 22 ነጥብ 2 በመቶ ዝቅ ብሏል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ፤ ባለፉት ዓመታት በተመዘገበው ዕድገት ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተቸሏል። በተለይም በከተሞች ውስጥ የነበረው ሥራ አጥነት ምጣኔ እየቀነሰ መጥቷል። ሆኖም አሁንም ድህነቱና ሥራ አጥነቱ ከፍተኛ በመሆኑ በቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገቱን በማፋጠን የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ የማሻሻልና በሥራ ሥምሪት ያላቸውን ተሳትፎ የማጠናከሩ ጉዳይ አሁንም ቅድሚያ ትኩረት ነው።

በዕቅዱ ለተቀመጠው የኢኮኖሚ ዕድገት ግብ መሳካት አንዱና ወሳኙ ጉዳይ የኢንቨስትመንት መስፋፋት ነው። ዕቅዱ ሰፋፊ ግቦችን ዕውን ለማድረግ የታለመ በመሆኑ የሚያስፈልገው የኢንቨስትመንት ፍላጎትና የፋይናንስ መጠን ከፍተኛ ነበር። ከዚህ አንፃር፤ የአገር ውስጥ ፋይናንስ አቅም እንዲጠናከር ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። በተለይም ዜጎች መቆጠብ እንዲችሉ የፋይናንስ ተቋማት እንዲስፋፉ በማድረግና የተለያዩ የቁጠባ ዘዴዎች ሥራ ላይ እንዲውሉና ዜጎችም በቁጠባ ላይ ያላቸው ግንዛቤ እንዲያድግ የተደረገው ጥረት አገራዊ ቁጠባ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ረድቷል። በዚህም ምክንያት ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ፍጥነት መስፋፋት መቻሉን የተገኘው የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንት መረጃ አመልክቷል። በ2006 በጀት ዓመት የኢንቨስትመንት ምጣኔን 40 ነጥብ 3፣ የቁጠባ ምጣኔን ደግሞ 22 ነጥብ 5 በመቶ በማድረስ፤ በዕቅዱ ከተያዘው ግብ በላይ አፈፃፀም እንዲያሳዩ ማድረግ መቻሉን የመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ያመለከታል።

ከ2008 እስከ 2012 ዓ.ም ተግባራዊ የሚደረገው 2ኛው የእድገትና ትራንስፎረሜሽን እቅድ አሁን ላይ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ሞልቶታል። የ2008ን ወይም የእቅዱን የመጀመሪያ ዓመት አፈጻጸም እንመለከት፤

የብሄራዊ ፐላን ኮሚሽን በቅርቡ ይፋ ባደረገው መግለጫ፣ በ2008 ዓ.ም የ11 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ ታቅዶ የነበረ መሆኑን አስታውሶ፣ ሆኖም የአገሪቱን 95 በመቶ የምርት መጠን የሚሸፍነው የመኸር ምርት በድርቁ ምክንያት በመቀነሱ የተቀመጠውን ግብ ማስመዝገብ እንዳልተቻለ አስታውቋል። የኮሚሽኑ መግለጫ በአገሪቱ ታሪክ ከ50 ዓመት ወዲህ ያጋጠመውን ከፍተኛ ድርቅ ተቋቁሞ የ8 በመቶ ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ማስመዝገብ መቻሉ በግብርናው ዘርፍ ላይ ጥገኛ የነበረው ኢኮኖሚ መጠነኛ መዋቅራዊ ሽግግር

ማድረጉን ያመለክታል፤ የሚል ማብራሪያ ሰጥቷል። በ2003 በጀት ዓመት ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው ውስጥ 44 ነጥብ 4 በመቶ ድርሻ የነበረው ግብርና በ2008 ዓ.ም ድርሻው ወደ 36 ነጥብ 6 በመቶ ዝቅ ማለቱን፤ በአንፃሩ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ወደ 16 ነጥብ 6 በመቶ፤ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፉ ደግሞ ወደ 47 በመቶ ከፍ ማለቱን የኮሚሽኑ መረጃ ያመለክታል።

በ2ኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የትግበራ ዘመን በመጀመሪያው እቅድ ዘመን ተጀምረው ሳይጠናቀቁ የቀሩ የስኳር ልማት፣ የሃይል ልማት፣ የባቡር መስመር ዝርጋታና መሰል ግዙፍ ፕሮጀክቶች ግንባታ ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል። እንዲሁም በ2ኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የተጀመሩና ይጠናቀቃሉ ተብለው የሚጠበቁ የውጭ ኢንቨስትመንትን መሳብና የወጪ ንግድን ማሳደግ ላይ ያተኮሩ የኢንደስትሪ ፓርኮች እንዲሁም የአግሮ ፕሮሰሲንግ ፓርኮች ግንባታ ተጠናቆ ወደስራ ይገባሉ። እነዚህ ዕውነታዎች በመስኖ ከሚደገፈው የግብርና ዘርፍ እድገት ጋር ተዳምረው በ2ኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዘመን ባለሁለት አሃዝ የእድገት እቅዱን ከማሳካት በተጨማሪ የመዋቅር ሽግግሩንም ማሳካት እንደሚቻል ያመለክታሉ። ይህን ፈታ አድርገን እንመልከተው።

ሃገሪቱ ትልቅ እምቅ አቅም ባላት የስኳር ልማት ዘርፍ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ትግበራ ዘመን 10 የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ግንባታ መጀመሩ ይታወቃል። እነዚህም በአማራ ክልላዊ መንግስት በጣና በለስ 3 የስኳር ፋብሪካዎች፣ በትግራይ ክልል የወልቃይት ስኳር ፋብሪካ፣ በአፋር የተንዳሆና ከሰም ስኳር ፋብሪካዎች፣ በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በኦሞ ሸለቆ 6 የኩራዝ ስኳር ፋብሪካዎች ናቸው።

እነዚህ የስኳር ፋብሪካዎች ግንባታቸው ተጠናቆ ወደስራ ሲገቡ የኢንደስትሪውን ዘርፍ እድገት በማፋጠን አጠቃላይ ኢኮኖሚውን ማሳደግ፣ መዋቅራዊ ሽግግሩንም ማሳካት ያስችላሉ። ፋብሪካዎቹ ግንባታቸው የተጓተተ ቢሆንም በቀጣይ አራት አመታት ይጠናቀቃሉ የሚል ግምት አለ። በተለይ በኦሞ ሸለቆ በመገንባት ላይ ከሚገኙት የስኳር ፋብሪካዎች ውስጥ የኦሞ ቁጥር አንድና ሁለት የስኳር ፋብሪካዎችን ግንባታ በቅርቡ ተጠናቆ ወደምርት ይገባሉ። የኦሞ ከራዝ ቁጥር አንድ እና ቁጥር ሁለት ፋብሪካዎች ግንባታቸው ከ90 በመቶ በላይ መጠናቀቁን የስኳር ኮርፖሬሽን ሰሞኑን አስታውቋል። እነዚህ ሁለት የስኳር ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ወደ ስራ ሲገቡ እያንዳንዳቸው በቀን 12 ሺህ ቶን የሸንኮራ አገዳ በመፍጨት 12 ሺህ ኩንታል ስኳር ያመርታሉ። የተቀሩት ስምንት የስኳር ፋብሪካዎችን ግንባታ በቀጣይ አራት ዓመታት በማጠናቀቅ አሁን በአገሪቱ ያለውን የስኳር ምርት ከ10 እጥፍ በላይ በማሳደግ ወደ 42 ሚሊየን ኩንታል ለማድረስ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም ኮርፖሬሽኑ አመልክቷል።

የሃገሪቱ ኢኮኖሚ እመርታዊ እድገትና ሽግግር እንዲያሳይ ጉልህ አስተዋጽኦ ባለው የኤሌትሪክ ሃይል ዘርፍም ውጤት እየተመዘገበ የገኛል። ኢትዮጵያ ከፍተኛ የታዳሽ ሃይል እምቅ አቅም ያላት ሃገር ነች። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከውሃ 45 ሺህ ሜጋ ዋት፣ ከንፋስ 10 ሺህ ሜጋ ዋት፣ ከከርሰ ምድር እንፋሎት 5 ሺህ ሜጋ ዋት፣ ከጸሃይ 119 ሜጋ ዋት የኤሌትሪክ ሃይል የማመንጨት አቅም አለ። በቅርቡ የተመረቀውን ጊቤ 3 ጨምሮ የሃገሪቱ የኤሌትሪክ ሃይል የማመንጨት አቅም ወደ 4 ሺህ ሁለት መቶ አድጓል። ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ጨምሮ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎረሜሽን እቅድ ትግበራ ዘመን የተጀመሩት የሃይል ማመንጫ ግንባታዎች ሲጠናቀቁ የሃገሪቱ የሃይል አቅም 10 ሺህ ሜጋ ዋት ይደረሳል።

ከዚህ በተጨማሪ የኢፌዴሪ የውሃ፣ መስኖና ኤሌትሪክ ሚኒስቴር በቅርቡ ይፋ ያደረገው መረጃ፣ ከታዳሽ ኃይል ከ5 ሺህ ሜጋ ዋት በላይ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት የሚያስችሉ 19 ፕሮጀክቶች በተያዘው በጀት ዓመት ማጠናቀቂያና በሚቀጥለው ዓመት ግንባታቸው ይጀመራል። ፕሮጀክቶቹ ከውኃ፣ ከፀሃይ፣ ከንፋስና ከእንፋሎት ኃይል የሚያመነጩ ናቸው። በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በትግራይና ሶማሌ ክልሎች ግንባታቸው የሚጀመረው ፕሮጀክቶች፤ ስምንት የውኃ፣ አራት የእንፋሎት፣ አራት የንፋስና ሦስት የፀሃይ ኃይል ማመንጫዎች መሆናቸውን ያመለከተው የሚኒስቴሩ መረጃ፤ ይህም ከውኃ 3 ሺህ 879፣ ከእንፋሎT 570፣ ከንፋስ 440 እንዲሁም ከፀሃይ 300 ሜጋ ዋት ኃይል የሚያመነጩ መሆናቸውን አስታውቋል። እነዚህ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ወደሰራ ሲገቡ የሃገሪቱ የሃይል አቅም ከ15 ሺህ ሜጋ ዋት በላይ ይሆናል።

ይህ የሃገሪቱ ሃይል ላይ የሚፈጠር እድገት በኢንደስትሪው ዘርፍ ሊመዘገብ የታቀደውን እድገት የማሳካት አቅም እንዲኖር ያደርጋል። እያንዳንዳቸው የአንድ ትልቅ ከተማን ያህል ሃይል የሚጠቀሙትን ሊገነቡ ለታቀዱ የኢንደስትሪ ፓርኮችና ሌሎችም ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን የሃይል ፍጆታ ማሟላት ከማስቻል በተጨማሪ የምስራቅ አፍሪካን በሃይል በማስተሳሳር ከሃይል ሽያጭ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ያስችላል። ይህ ኢትዮጵያን የቀጠናው የሃይል ማዕከል ያደርጋታል።

የኢንደስትሪ ፓርኮች ግንባታ፣ አጠቃላይ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ በተለይ የኢንደስትሪውን ዘርፍ የኢኮኖሚ መዋቅር ሽግግር ማምጣት በሚያስችል አኳኋን ያሳድጋል ተብሎ ይታመናል። የኢንደስትሪ ፓርኮች፤ ኢንቨስተሮች መሰረተ ልማት የተሟላለት የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ከማድረግ ባሻገር፣ ከመሬት ጥያቄና ከግንባታ ጋር የተያያዙ ውጣውረዶችን ስለሚያቃልሉ ዘርፉን ለኢንቨስትመንት ምቹና አበረታች ያደርገዋል። በቅርቡ በሃዋሳ ከተማ ተገንብቶ ካተመረቀው በወጪ ንግድ ላይ ያተኮረ የጨርቃጨርቅ ኢንደስትሪ ፓርክ በተጨማሪ በአዳማ፣ በመቀሌ፣ ደሬዳዋና ኮምቦልቻ ከተሞች ተመሳሳይ የኢንደስትሪ ፓርኮች በመገንባት ላይ ይገኛሉ።

ከዚህ በተጨማሪ በክልላዊ መንግስታት በኮርፖሬሽን ደረጃ የሚመሩ የግብርና ማቀነባበሪያ የኢንደስትሪ ፓርኮች ግንባታም የማከናወን እቅድ ተይዞ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተጀምሯል። ከእነዚህም መካከል በትግራይ ሁመራ፣ በኦሮሚያ ቡልቡላ፣ በደቡብ ይርጋለምና በአማራ ቡሬ አካባቢዎች የሚገነቡ የተቀናጁ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ዋንኞቹ ናቸው። እነዚህ የግብርና ማቀነባበሪያ ኢንደስትሪ ፓርኮች፣ ሀገሪቱ ሰፊ የግብርና እምቅ አቅም ያላት ያላት ከመሆኑ አንጻር፣ በግብርና ማቀነባበሪያ የሚሰማሩ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ የግብርና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር በሀገር ውስጥና በውጪ ገበያ እንደሚሳተፉ ማድረግ ያስችላል።

ያለቀልጣፋ፣ ፈጣንና አዋጭ የትራንስፖርት አገልግሎት የኢኮኖሚ እድገትን በሚፈለገው ደረጃ ማሳካት አይቻልም። በተለይ በየብስ ትራንስፖርት ዘርፍ የባቡር ትራንስፖርት በዚህ ረገድ ትልቅ ድርሻ አለው። የኢፌዴሪ መንግስት ለዚህ ዘርፍ ልማት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል። ከአዲስ አበባ እስከ ጅቡቲ ከተዘረጋውና በቅርቡ ከተመረቀው የባቡር መስመር በተጨማሪ፤ የመቀሌ አዋሽ፣ ወልዲያ ሃራ ገበያ የባቡር መስመር በግንባታ ላይ ይገኛል። እስካሁን ባለው ሂደት ግንባታው በከፊል ተከናውኗል። ይህ የባቡር መስመር አዋሽ ላይ ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ከተዘረጋው መስመር ጋር ይገናኛል። ከአዲስ አበባ ወደደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ እስከ ቤዴሌ የሚገነባውም የባቡር መስመር የገንዘብ ምንጭ ተገኝቶለት ለግንባታው የመሰረት ድንጋይ ተጥሏል። ይህ በተለይ በኢሉአባቦር ዞን በመገንባት ላይ ከሚገኘው የያዩ ማዳበሪያ ፋብሪካ ጋር ስለሚገናኝ በመላው ሃገሪቱ በተመጣጣኝ ዋጋ ማዳበሪያ እንዲቀርብ በማስቻል የሃገሪቱ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ላይ የጎላ ድርሻ እንደሚኖረው ይታመናል። ሌላው ሊገነባ የታቀደው የባቡር መስመር ከወልዲያ ተነስቶ ሃገሪቱን ታጁራ ከተሰኘው የጅቡቲ ወደብ ጋር የሚያገናኝ ነው።

እነዚህ ከብዙ በጥቂቱ የጠቃቀስናቸው የልማት ፕሮጀክቶች የአገሪቱን ፈጣን እድገት ቀጣይነት፣ የመዋቅር ሽግግሩን እውን መሆንና በአጠቃላይ በ2017 የአገሪቱ ኢኮኖሚ ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ደረጃ ላይ መድረሱ አይቀሬ መሆኑን ያረጋግጣሉ። ይህ ኢትዮጵያን በአፍሪካ፤ በተለይ በምስራቅ አፍሪካ ባለግዙፍ ኢኮኖሚና ተጽእኖ ፈጣሪ ያደርጋታል። ይህም ብዙዎች ማለት እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ መጪዋ “የአፍሪካ አንበሳ” መሆኗ አይቀሬ መሆኑንም ያመለክታል።